# ረቂቅ ህግ HR2003 (ወይም የሰብኣዊ መብት ድንጋጌ 2003) ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዴት “ብቸኛና ሁነኛ መፍትሄ” ሊሆን ይችላል?

ለኣከ ገብረፃድቅ
መስከረም 25 2000 ዓ ም

ዲሞክራሲን በኣመሪካ ህገ መንግስት ኣመካኝነት በኢትዮጵያ ላይ የሚደነግግ HR2003 የተባለው ረቂቅ የኣመሪካ መንግስት የተወካዮች ምክር ቤት ባለፈው ሳምንት ማፅደቁ ይታወቃል።

የዚህ ፅሁፍ ኣላማ የረቂቁ ይዘት፣ ያስነሳው የሉኣላዊነት ጥያቄና፣ በዙርያው ያለ የኣማላጆቹና ደጋፊዎቹ እምነትና ኣስተሳሰብ ምን እንደሚመስል ያለኝን ግንዛቤ ለመግለፅ ነው። ረቂቁንና ኣባሪ መግለጫዎች ከተመለከትኩ በኋላ ያገኘሁትን ግንዛቤ በሚለካ ኣኳሃን በግልፅና ጠንካራ ኣንደበት ከዚህ በታች እተቸዋለሁ።

**ሀ- ከረቂቁ ህግ በላይ ዋናው ችግር የተበከለው የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ግንኙነት ነው፤**
HR2003ና ሌሎች በኢትዮጵያ ላይ ኣጠያያቂ የሆኑ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች (በህብረተሰቡ ክፍፍል መፈጠርን ጨምሮ) ባለው የፖለቲካ ጠበኝነት የተነሳ ከነፃ ውይይት ውጭ ስለሚደረጉ በየኣቅጣጫው የኣገሪቱን ውድቀት ሲያቀላጥፉ ይታያሉ።

ረቂቁ ለብዙ ጊዜ ትኩረት ኣጥቶና ግልፅ ከሆነ የፖለቲካ ውይይት ተሰውሮ በመቆየት ከቅርብ ሳምንታት ወዲህ መሰረታዊ የሉኣላዊነትና ሌሎች ጥያቄዎችን መቀሰቀሰ ጀምሮኣል። ለዚህም ዋና ምክንያት በመንግስት ተቃውሞ ጎራ በመደራጀት የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ካላቸው የፖለቲካ ባህሪ የተነሳ ስርኣት ያለው ውይይት የማይቻል በማድረጋቸው ነው። ወገናዊ ፖለቲካን ሰለሚያራምዱ ማንኛውም የሚፃረራቸው ነፃ ኣስተያየት በ”ወያኔ” ደጋፊነት በመፈረጅ በፀብ፡ በኣመፅና በስድብ ይጋፈጡታል። የኢትዮጵያ ፖለቲካም የመንግስትና ተቃዋሚዎቹ ባላንጣ ካድሬዎች ብቻ ሳይሆን የደጋፊዎቻቸውም ጭምር ኣስኮናኝና ያዘቀጠ ባህል ፍልምያ ሆኖ በመቅረቱ በውይይት የሚፈቱ የፖለቲካ ችግሮች ወደ ቀውስ በመቀየር ስያባብሱት ይታያሉ።

በተለይም እንደ ድረ-ገፅና ረድዮ የመሰሉ ዜና ማሰራጫዎች በነዚሁ የተቃዋሚ ድርጅት ካድሬዎችና በደጋፊዎቻቸው ድጎማ በኣንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢህወደግ ካድሬዎች በመንግስት በጀት ቅጥረኝነት የሚቆጣጠሩዋቸው በመሆኑ ነፃ ኣመለካከት ላላቸው ኢትዮጵያውያን የውይይት መድረኮቻቸው ኣስፈሪና ዝግ ናቸው፤ በቅንነት ስለ ኢትዮጵያ የሚከራከሩ ነፃ ኣመለካከት ያላቸው ወገኖችም የራሳቸው ነፃ የሆነ መድረክ ለማቆም ብቁ ድርጅትና እንቅስቃሴ የመፍጠር ጠንካራ ህሊና ያላቸውም ኣይደሉም።

ለረጅም ጊዜ ረቂቁን በብቸኝነት ሲቃወም የቆየው የኢትዮጵያ መንግስትና በውጭ የሚገኙ ካድሬዎቹ ናቸው። የኢህወደግ መንግስት ራሱ የኢትዮጵያ ሉኣላዊነት በዘልማድ በክህደት ሲንድ የቆየ ስርዓት በመሆኑና ተቃውሞው ቅንነት የሌለው፣ ስልጣኑን ለመከላከል የሚያካሂደው የፕሮፓጋንዳ ሥራ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ሊጋሩት ኣልቻሉም። ከህዝብ ድጋፍ የተነጠለው የኢህወደግ መንግስት በመቶ ኣእላፍ ዶላር የቀጠራቸው የኣመሪካ ነገረፈጂዎች ሳያሳኩለት ሲቀር ይኸውና ተመልከቱ ሻዕብያና ኣበሮቹ የሚያደርጉት፣ ድምፃችሁን ኣሰሙ እያለ በAigaforum.com ስለ ሉኣላዊነት በኢትዮጵያውያን ላይ መመፃደቅ ጀምሮኣል።

ይሁንና የተባለው ረቂቅ ህግ የኣገሪቱ ሉኣላዊነት የሚጋፋና መዘዝ የሚያስከትል በመሆኑ ጉዳዩን ያሳሰባቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያን በግላቸው ያደረባቸው ስጋትና ቅሬታ መግለፃቸው ኣልቀረም።

**ለ- በረቂቁ ዙርያ ያለ የተዛባ ኣስተሳሰብ**
በኔ ኣስተያየት ዲሞክራሲን ከኣንድ ኣገር ማለትም ከኣመሪካ ጋር እንደማይለያዩ ኣንድ ኣካል በማቆራኘት የሌሎችም ኣገሮች የፖለቲካ ችግር ከዚህ የተሳሳተ ኣስተሳሰብ ኣንፃር ማየት ኣደገኛ ነው።

በረቂቁ ዙርያ የሚንቀሳቀሱ አማላጆችና ደጋፊዎች የሚያንፀባርቁት አስተሳሰብ ስንመለከት ይህ ረቂቅ ለኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርዓት እጦት መፍትሄ እንደሚሰጥ አድርገው ይሰብካሉ። ቅንጅት ለHR2003 የተባለው ረቂቁን በአመሪካ መንግስት ምክርቤት የሚያማልደው የኢትዮጵያውያን ቡድን በፈረንጅ አቆጣጠር መስከረም 27፤ 2007 ባወጣው መግለጫ "ዶናልድ ፐዪን የነፃነት፣ ዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት ለኢትዮጵያ ገፀበረከት ሰጡ" በሚል ርእስ ለኢትዮጵያ ህዝብ የጥገኝነት ስነልቦናን የሚሰብክ አሳፋሪ መግለጫ አውጥቶአል። (http://www.ethiopianreview.com/articles/1216 ተመልከቱ)። ቡድኑ ረቂቁን ለኢትዮጵያ እንደ መጨረሻ እድል መፍትሄ አድርጎም ያምንበታል። ባወጣው ሌላ የጥያቄና መልስ ማብራርያው ላይ (ገፅ 2) "ለምን ይህ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ጠቃሚ ሆነ?" ለሚለው የራሱን ጥያቄ ሲመልስ "ምክንያቱም የኢትዮጵያ ገዢው መደብ የአለም አቀፍ ሰብአዊ መብትና ህግን ለማክበር የሚያስገድደው ይኸው ረቂቅ ሁነኛና (እርግጠኛ ወይም ጭብጥ ለማለት ነው) ብቸኛ መፍትሄ ሰለ ሆነ ነው" ይላል፤ (በአማርኛ የተሰጠ ትርጉም ከእንግሊዘኛው የራቀ በመሆኑ የራሴ ትርጉም)። አለፍ ብሎም [ረቂቁን በአመሪካ መንግስት እንደ ህግ እስኪፀድቅ ድረስ ማለቱ ነው] "መሬት በዛብያዋ እንደተመላለሰች ሁሉ ፀሃይ ብርሃንዋ እስከፈነጠቀች የኛም የማያቋርጥ ትግል ይቀጥላል" ይላል (http://www.hr5680.org/HREngAmh.pdf ተመልከቱ)። በእርግጥም በኢትዮጵያ ዲሞክራስያዊ ስርዓት ከህዝቡ ትግልና የፖለቲካ ድርጅቶች መማር ከሚገባቸው የዲሞክራሲ ባህል ለማጎልበት የሚደረግ ለውጥ ረቂቁን በሚደግፉ ሰዎች አስተሳሰብ ዘንድ ፋይዳ የሌለው እንደሆነ ያመለክታል። ለዚህም ይመስላል የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርዓት ምስረታ እድል በHR2003ና በረቂቁ አካባቢ ያሉ ሰዎች ብቻ እንደተወሰነ አድርገው የሚያቀርቡት።

የዲሞክራሲ መርህና ግብ ያልነበረው ቅንጅት የፖለቲካ ውድቀት ከ1997 ምርጫ በኋላ እዉን እየሆነ ከመጣ ወዲህ የኢህወደግ መንግስት ጠላቶችና ደጋፊዎቻቸው HR2003ን የህዝቡን የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ የሚተካ እንደ ዋና የትግል ስትራተጂ አድርገው መመልከት ጀምረዋል። የቅንጅት የፖለቲካ ውድቀትም በኢህወደግ ላይ በማላከክ የፖለቲካው ውድቀት ራሱ የቻለ ፖለቲካ ሆኖ በደጋፊዎቹ ጀርባ (ማለት በገንዘብና ሞራል ድጋፍ) ሲንሸራሸር ይታያል። መሪዎችም ገዢውን ድርጅት በዲሞክራስያዊ ትግል ሂደት ከመፈታተንና ከህዝቡ ያስነጠቁትን ከፊል መብቶች እንኳ ማስመለስ ከመጣር ይልቅ አገሪቱንና የኢትዮጵያ ህዝብን ወደኋላ ትተው ወደ ውጭ አገር በመንጋጋት ተሰፋቸውና ተጠሪነታቸው እጅጉን ጎሳዊ አክራሪነት ለተጠናወታቸው በውጭ ለሚኖሩ ከፋፋይ የፖለቲካ ቡድኖች አድርገዋል። እርስ በርስ የመባላቱ ኩተታቸውም እንዳለ ወደ ውጩ አለም እየጎተቱት መጥተዋል። ከዚህ የተነሳ በአገር ውስጥ መካሄድ ለሚገባው ዲሞክራስያዊ እንቅስቃሴ የሚያዳክመውን የሰመድ2003 ረቂቅ ዲሞክራሲን ከባእድ አገር ታሽጎ እንደሚመጣ ብርቅ እቃ ለኢትዮጵያ ህዝብ አጕል ተሰፋ ለማስነቅ እየሞከሩ ነው፡፡

ሌላው በዚሁ ረቂቅ ዙርያ በተሰባሰቡ ደጋፊዎች ያለው መና አስተሳሰብ "አመሪካ ሃያል ዲሞክራስያዊት አገር ስለሆነች በአለም ደረጃ ዲሞክራሲን የማስፈን በጎ ፍላጎትና ሃላፊነት አለባት" ብለው ከልብ ስለሚያምኑ ለረቂቁ የሚያደርጉት ድጋፍና ኢትዮጵያ ውስጥ ለመመሥረት ሰለሚደረገው የዲሞክራሲ ስርዓት ይህን የተሳሳተ አስተሳሰብ መሰረት ያደረገ ነው። ሃቁ ግን ለስልጣን የሚበቃ ማንኛውም የአመሪካ መንግስት የውጭ ፖሊሲውን ከጥቅሙ አኳያ ከማራመድ ሌላ አላማ ኖሮት አያውቅም። እንድያዉም የቅርብ ታሪክ እንደሚመሰክረው የአመሪካ መንግስት ጣልቃ የገባባቸው አገሮች ሁሉ ከመታመስ በቀር ዲሞክራሲ ይቅርና መረጋጋት እንኳ አይታይባቸውም።

በተለይም የዚሁ ህግ ረቂቅ ዋና መነሻ ፅንሰ ሃሳብ የኢትዮጵያ መንግስት ለሚፈፅማቸው ኢሰብአዊ ተግባራት ተጠያቂነቱ ለአገሪቱ ህግና ለኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑ ቀርቶ ለአመሪካ ግብር ከፋይና የሚወክለው ባእዳዊ መንግስት ያደርጋል። በእርግጥ ይህ ህግ የኢትዮጵያ ባለስልጣናት የሚፈፀሙት ወንጀል እንደ ተራ ነገር ከእርዳታና እርጥባን ጋር በማቆራኘት የተጠያቂነትን አላማ የሚፃረር እንጂ የህግ ተጠያቂነትን የሚያጠናክር አይደለም።

**ሐ- በረቂቁ ዙርያ ያሉ ግለሰቦችና የኢትዮጵያ ተፃራሪ ሃይሎች**

በመጀመሪያ ቅንጅት ለHR2003 ሚናው ምን እንደሆነ ልጥቀስ። የHR2003 በኩር ረቂቅ HR4423 አርቃቂ የሪፓብሊካኑ ክሪስቶፈር ስሚዝ ናቸው። ከዛም በኋላ ዶናልድ ፐዪን እንደተቀላቀሉበተና በዚሁ ጉዞ ሌሎችም ፀረ-ኢትዮጵያ አመለካከት አካላት ሲንቀሳቀሱበት ቆይተዋል። ከላይ በስሙ እንደጠቀስኩት ቅንጅት ለHR2003 ዋናው ስራው የአመሪካን መንግሥት ረቂቁን በተመለከተ

ማማለድ ነው። ሌላው ዋናው ስራው ረቂቁን በዋናነት ለሚገፉት ሃይሎች ከኢትዮጵያ ማህበረሰብ ድጋፍ ለማሰባሰብ የህዝብ ግኑኝነት የውክልና ስራ ነው። ቡድኑ በድረ-ገፁ ተልእኮውን ሲገልፅ እንደሚከተለው ያስቀመጣል፣ "Provide a clearinghouse for information and materials on H.R. 5680 and related legislative activity…" ወይም "ኤች ኣር 5680ን (የረቂቁ ኣሮጌ መጠርያ) በማፅደቅ ተግባር የሚቀርብ የመረጃና ቁሳቁስ ማደራጃ ቤት ሆኖ ማገልገል" ማለት ነው።

እዚህ ማስመር የምፈልገው ነጥብ ይህ ረቂቅ ህግ ከሁሉም ጣልቃ ገብ ሃይሎች ነፃ የሆነ በኢትዮጵያውያን የተነደፈና ኢትዮጵያዊ ሰብኣዊ መብት ኣላማ ያለው እንቅስቃሴ ኣይደለም። የመጀመርያ ጊዜ ታዛቢ በረቂቁ ላይ የሚኖሮው ግንዛቤ፣ ቅንጅት ለHR2003 ራሱ ያነሳው የኢትዮጵያ የሰብኣዊ መብት ኣላማ የሚያራምድ እንደሆነ ኣድርጎ ረቂቁን በባለቤትነት ይናገርበታል። ቡድኑ ቀና ኣላማ ሊኖረው ይችላል። ዋናው ችግር ቡድኑ ረቂቁን እንደኣላማው ወስዶ መታገሉ ሳይሆን ህጉን በመጠቀም በፀረ-ኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱበት ሃዪሎች መኖራቸውና መንገድ ከፋች መሆኑ ነው።

ኮንግረስማን ዶናልድ ፐዪን በሊቀመንበርነት የHR2003ን ምስክርነት ሲያዳምጡ በቪድዮ ተከታትያሎህ። ረቂቁ ከኤርተራ ጉዳይ የሚያገናኝ ነገር ባይኖረውም የኤርትራ ኣሸባሪ ተግባራት በተነሳ ቁጥር በተደጋጋሚ ለኤርትራ ሲከላከሉ ወገናዊነታቸው በገሃድ ስለነበር ኣንድ መስካሪን የመዝለፍ ኣሳፋሪ ኣመል ሲያሳዩ ነበር። ለዚህም ያክል "ኤርትራ በኣሸባሪነት የምትመደብ ከሆነ ኢትዮጵያም ትግባ" ብለዋል። በእርግጥ ኢህወደግን ለማስገደድ ሹል መንጋጋና ጥፍር ያለው ህግ HR2003 ሳይሆን ኢትዮጵያን በኣሸባሪነት የሚመድብ ህግ ማውጣት ነው። የሚከተለው ውድቀት ግን ጭራሽ በኢህወደግ ባለሥልጣናት ሳይሆን በኣገሪቱ ላይ ነው።

በተለያየ ወቅትም ስለ ኤርትራ የድንበርና ሌሎች ጉዳዮች በጥብቅና ሲከራከሩ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውም መሰረታዊ ችግር ሊደብቁት የሚቻላቸው ኣይደለም። እንዲህ ኣይነቱ ግለሰብ ማእከላዊነት ይዞ የሰብኣዊ መብት ተጣባቂ ሊሆን ኣይችልም። በእርግጥ ያሉበት ሥራም ወገንተኛነትና የፖለቲካ ነገረፈጂነት ነው።

ይህ ወገናዊ ኣመለካከት በዶናልድ ፐዪንና ከሳቸው ጋር በቅርበት የሚሰሩ ኣንድኣንድ ኢትዮጵያውያን ገለሰቦች ላይ የተወሰነ ኣይደለም። ብዙ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች የኤርትራ መንግስት እንደ ትግል ኣጋራቸው ኣቅፈውታል። የራሳቸውን ወገን የትግራይን ህዝብ በጠላትነት በመመደብ የኢህወደግ መንግሥት በብቀላ ለመንቀል ያህል ከኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጠላቶች ማበር ዋና የፖለቲካ ስትራተጂኣቸው ነው። የኤርትራ መንግስት በኣባታውነት ያቆመውና በቀጥታ የሚደግፋቸው በADF የታቀፉ የቃል ኪዳን ድርጅቶች ቅንጅትን (CUD) ጨምሮ በኢትዮጵያ ላይ እያሳደረ ያለው የተካነ ኣሉታዊ የፖለቲካ ተፅእኖ በየቀኑ የምንከታተለው ጉዳይ ነው። ኤርትራ የተገላብጠሽ የኢትዮጵያንና ህዝብዋን የፖለቲካ እድል እንድተወስን (EPPF፣ ONLF፣ OLF፣ ወዘተርፈ ወታደረዊ ስለጠና ሳይቀር) መቀበል ኢትዮጵያዊነትን በሃፍረት የሚያከናንብ ተግባር ነው።

ሌላው በግልፅ ፖለቲካዊ ወገንነታቸውን የለዩ የመነግሥት ተቃዋሚ ግለሰቦችና ካድሬዎች ራሳቸውን የሰብኣዊ መብት ተካራካሪ የሚል ስያሜ በመስጠት ሰሞኑን እንደ ኣሸን ፈልተዋል። የሰብኣዊ መብት ተከራካሪ ለመሆን ራስን ከፖለቲካዊ ኣድልዎ ማግለልና ቀደምት ኣላማ የሰብኣዊ መብትን ጥያቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ሌላው መንገድ ደግሞ በኣገር ወዳድነትና በኣርበኝነት የትኛውም የፖለቲካ ድርጅት እንደ ቁምነገሩ በመቀበለና በድከመቱ ደግሞ በመውቀስ ወይም በመተቸት ነፃ ኣቋም ይዞ ለዲሞክራሲ መታገል ነው።

የሰብኣዊ መብት ጠበቃነት ተልእኮ ከተነሳ ዘንድ የመንግስቱ ሃይለማርያምን ስም በረቂቁ ሰለመካተቱ እንመልከት። በረቂቁ ዙርያ ያሉ ኣካላትና ግለሰቦች (የቀድሞው የፕሮፌሰር መስፍን ወለማርያም የሰብኣዊ መብት ድርጅት ጨምሮ) የሰብኣዊ መብት ጥብቅና ዋና ኣላማቸው ቢሆን ኖሮ መንግሥቱ ሓይለማርያም እንደ ጀግና መታየቱ ቀርቶ (እንደ ጀግና ከልባቸው ያስቀመጡና ስእሉን በደረታቸው ለጥፈው የሚሄዱ ኣሉና) ተገቢዉን ፍርድ እንዲያገኝ ውጭ ኣገር ካሉ ነበሰገዳይ ካድሬዎቹ ጋር ወደ ኣገር ተመልሶ ተገቢውን ፍርድ እንዲቀበል ለ20 ኣመታት በላይ በታገሉ ነበር። ከዚህ በተቀረ መንግስቱ ሃይለማርያምን ከኣገር በማሸሽ በስተጀርባ ዋና ተባባሪ የነበሩት ኣንዱ ኣሁን የሚማልዱት የኣመሪካ መንግስት ነው።

ያን ያህል ወንጀል በኣገርና ህዝብ ላይ የፈፀሙ መንግስቱና ኣበሮቹ በድሎት እየኖሩ ለይስሙላ ያህል በዚሁ የሰብኣዊ መብት 2003 የተሰኘ ረቂቅ (ክፍል 4 ቁጥር 6) ስሙን ማካተታቸው በተፈፀመው በደል መቀለድና የቅሌት ተግባር ነው። ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ሰላምና ፍትሓዊ ስርኣት ይኖራል ብሎ መገመት የሚቻለው ካለፈው ኣምባገነን መንግሥት ቅሪቶች ጋር ሆኖ በኣሁኑ ኣመባገነን ላይ ኣብሮ መፈክር ማሰማት ሳይሆን ያለፈውን በደል በቅድሚያ ፍትህ እንዲያገኝ በመታገልና ከግብ በማድረስ ነው። ያ ቢሆን ኖሮ ለመለስ ዜናዊ መንግሥትም ትምህርት በሆነ ነበር። ያ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ ቅንጅት ለሚፈፅማቸው የፖለቲካ ስህተቶች ያለ ምንም ትችትና ነቀፌታ፣ በተለይም ረቂቁ ህግ እንደሚያሰምረው ያለ ምንም "ተጠያቂነት" በጀርባ እሽሩሩ ብሎ ወደ ስልጣን ማውጣት ለሌላ ኣምባገነናዊ ስርኣት የሚደረግ ዝግጅት ከዛም ኣልፎ ያለፈውን ቁስል ላይ በቂምበቀልነት ሽካል የመስደድ ኣደገኛ እንቅስቃሴ ነው። ይህም የምለበት ምክንያት ግልፅ ነው። የቅንጅት ደጋፊ ካድሬዎች እንዲሁም ጭፍንና ወገንተኛ ተከታዮቻቸው ስህተት እየፈፀማችሁ ነው ብለው የመተቸት ባህሉ ወይም ፍላጎቱ የላቸውም። ይልቁንም መሪዎቹን በማይገባ ቃላቶች ይክቡዋቸዋል። ዋናው ቅሬታቸው ለምን ይኸን የኢህወደግ መንግስት ለመጣል ትብብርና ቅንጅት ኣይኖርም ብቻ ነው።

***መ- የረቂቁ ህግ የኢትዮጵያን ሉኣላዊነት ይጋፋል***

እዚህ ላይ ሉኣላዊነትን ይጋፋል ስል የኢህወደግን መንግሥት ከስልጣን ለማስወገድ በሚል ሰበብ ህገወጥ እንቅሰቃሴን እንደ ህጋዊ መቀበል ስህተት መሆኑ ለማመለካከት ነው። የኣገርን ሉኣላዊነት ለመድፈር ጦር መስበቅ ወይም ድንበርን መርገጥ ኣያስፈልግም። ከጦርነት በፊት ወደ ጦርነት ሊያመሩ የሚችሉ ተራ መሰል የመብት መጋፋት ውጥረቶች ይከሰታሉ።

HR2003 የኢትዮጵያን ሉኣላዊነት ስለ መጋፋቱ በቀለለ መንገድ ለማስቀመጥ ያህል በኣመሪካ መንግስት እጅ መሆኑ ቀርቶ በተባበሩት መንግስታት ወይም በኣፍሪቃ ኣንድነት ቢሆን ኖሮ ህጋዊነቱና ተቀባይነቱ ግልፅ በሆነ ነበር። የኣመሪካ ሓያልነት ወደ ጎን በመተው በዓለም ማህበረሰብ እንደ ሌሎች ኣገሮች በእኩልነት መታየት ያለባት ሲሆን፣ ሃያል ኣገር እንደ መሆንዋ መጠን ግን ከማንኛውም ኣገር ጥቅም ጋር፣ ከኢትዮጵያም ጨምር የሚኖራት የሚጋጭ የውጭ ጉዳይ መርህና ጥቅም ይበልጥኑ ጉልህ ይሆናል።

በኔ ኣስተያየት እንዲህ ኣይነት ኣላማ ያለው ረቂቅ የኢትዮጵያን ሉኣላዊነት ሳይጋፋ መተግበር የሚገባው በሁለቱ መንግሥታት በሚደርጉ የኢኮኖሚ ስምምነቶች ውስጥ ብቻ ሲታከሉ ነው።

ቡድኑ ረቂቁን የሚቃወሙትን በጥያቄና መልስ መግለጫው ሲገልፃቸው (በገፅ 4-5) ኣብዛኞቹ በድፍን ካለማወቅ፣ የሕግ ቃላቶችን ካለመረዳትና (የመንግስት ደጋፊዎችን ጭምር) ለማደናገር የሚያደርጉት ምክንያቶች ነው ይላል። የተቀረው ማብራርያ ዘለፋ ብቻ ነው። በዚህ ኣይነቱ ኣምባገነናዊ ኣመለካከት መረዳዳት ሊፈጠርና ዲሞክራሲን መመስረት ኣይቻልም።

የኢትዮጵያ መንግሥት በረቂቁ ህግ ላይ የሚያቀርበውን የሉኣላዊነት መደፈር የተቃውሞ ክስ ሲያስተባብል፣ መንግስት ራሱ ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ኣገሪቱን ጥገኛ ያደረገ የበጀት ድጎማ ከኣመሪካ መንግስት በመቀበል የኣገሪቱን ሉኣላዊነት ኣመንምኖት እያለ እንዴት ረቂቁን ህግ ሉኣላዊነትን ይጋፋል ማለት ይችላል ይላል (በገፅ 4)። በእርግጥ እንደዛ ሲል HR2003 የሰው ኣገር ህግና ጉልበት በጥገኝነት በመማለድ የባሰውኑ የኢትዮጵያ ሉኣላዊነትን እንደሚንድ ያመለክታል። በነዚህ ባላንጣ ሃይሎች ስህተቶች ሲደጋገሙ ለኢትዮጵያ የሚጎዳ እንጂ የሚረዳ እውነታ ኣይወጣቸውም። የረቂቁ መግለጫ የኢህወደግን ቅዋሜ ወደ ጎን ትቶ ከመንግስት ነፃ የሆኑ ግለሰቦች ያላቸውን ስጋት ምላሽ መስጠት ይቅርና የኣገር ሉኣላዊነትን እንደማይጋፋ ለራሱ ደጋፊዎች ለመግለፅ በራስ-ኣነሳሽነት ምንም ጥረት ኣያደርግም።

የኣመሪካ ኮንግረስ በHR2003 ኣመካኝነት ኢትዮጵያን ለይቶ ለማጥቃት ያለመ ነው ወይ ብሎ በመጠየቅ (በገፅ 3) የሚመልሰውን እንመልከት። ኣይ የለም፣ ቬትናም፣ ዳርፉር፣ ኢራንና ሌሎችን የሚመለከቱ ተመሳሳይ ህጎች ኣሉ ይላል። "የኢራን የነፃነት ድጋፍ ድንጋጌ" በመባል የሚታወቀው ህግ ብንወስድ የኢራንን ፀረ-ኣመሪካ ኣቋምና የኑክሌር መሳርያ ስራዋን ለመግታት በኣመሪካ መንግስት ግፊት የረቀቀና የፀደቀ ነው። በኣስባቡም የኢራን ተቃዋሚ ድርጅቶች ዲሞክራሲን

በማመካኘት የኢራንን መንግስት ለማዳከም እንዲረዱበት የታለመ እንጂ የአመሪካ መንግስት ለኢራን ሰብአዊ መብት ተቆርቍሮ ያወጣው ህግ አልነበረም። በመሰከረም 2005 ፈረንጅ የፀደቀው ይህ ህግ ፕረዚደንት ቡሽ በቅርብ የሚከታተሉት ጒዳይ ስለ ነበር ጉባኤው እንዲያፀድቅላቸው ሲማፀኑ ቆይተው በፀደቀም እለት አድናቆታችውን መግለፃቸው ጒዳዩ ሰለ አመሪካ ጥቅም እንጂ ስለ ኢራን ዲሞክራሲ አልመሆኑ ግለፅ ነው።

እዚህ ላይ HR2003ን ለማፅደቅ ከኢትዮጵያ ወገን በመግፋት ላይ ያለው ቡድን የኢትዮጵያ ሉኣላዊነት ከሌሎች ኣገሮች የማይዛመድ ሁኔታ ጋር በግድየለሽነት ወይም በደፈና በማደባለቅ የባእዳውያን ጣልቃ ገብነትና ሉአላዊ ድፍረት የተለመደ ተራ ነገር እንደሆነ በማድረግ ማቅረቡ ኣግባብ ወይም ብልህ ነገር ኣይመስለኝም።

**ሠ- HR2003 ሊያስገኘው የሚችል ውጤት**

የተጠቀሱት ጣልቃ ገብ የአመሪካ ህጎች በምንና ማን ኣነሳሽነት እውን እየሆኑ ነው ወይም ያስገኙት ውጤትስ ምንድነው ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ከወዲሁ መተንበይ ይቻላል።

HR2003 በጥራዝነጠቅነት የሚጠቀምበት "ተጠያቂነት" የሚለው ቃል ብንመረምር ባለስልጣናትን በተጠያቂነት የመያዝ አቅም የለውም። ምክንያቱም ያን ውጤት ለማስገኘት ወንጀል ሲፈፅሙ ወደ ሕግ ለማቅረብ ኣፈፃፀሙን የሚተገብር የበላይ ተቆጣጣሪ መዋቅርና አካል ይጠይቃል። ካሉት የኢትዮጵያ ኣስፈፃሚ ኣካላት መዋቅር በላይ ሌላ ተደራቢ ኣካል እንዴት ሊኖር ይችላል? እንድያውም ይህ ረቂቅ የበላይ ባለሥልጣናት ለበታች ባለስልጣናት ያልተገለፀ ድፍን ሥልጣን በመሥጠት ለሚፈፀሙ ወንጀሎች የበላይ ባለሥልጣናትን ከተጠያቂነት ነፃ ሊያወጣ ይችላል። በመሰረቱ ረቂቁ ገና ከወዲሁ የበላይ ባለሥልጣናትን ከተጠያቂነት ነፃ ኣድርጎዋቸዋል። ምክንያቱም የበላይ ኣስፈፃሚ ኣካላት ናቸውና።

ባለስልጣናቱ ስልጣን ሲከዳቸው የዘረፉትን ዘርፈው ከኣገር ይፈረጥጣሉ። ከፈረጠጡ በኋላ ግን ቅንጅት ለHR2003 ቡድን ይሁን ረቂቁ በተጠያቂነት የሚይዛቸው ኣንቀፅ ወይም ተከታታይ እርምጃ የላቸውም። ስለ ምንስ ይሆን ረቂቅ ህግ HR2003 በወንጀል የሚጠየቁ ባለስልጣናት (የእርዳታ ገንዘብን በማባከን የሙስናን ወንጀል የሚፈፅሙ ጭምር) በውጭ ያጋዙት የኣገር ሃብት (የባንክ ሂሳብና ንብረት) እንዲታገድና ለባለቤቱ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚመለስበት ኣንቀፅ ያላካተተው? ይህ የቀድሞው የሃይለስላሴና መንግስቱ ሃይለማርያም ባለ ስልጣናትንም ይመለከታል። ኣማላጅ ቡድኑ በዚህ በኩል ያለው ሥልጣንና ራእይ እንተውና እንዲህ ኣይነቱ እርምጃም በኣመሪካ ወይም ኣውሮጳ መንግሰታት የሚፈለግ ኣይደለም።

በኣንፃሩ የኢትዮጵያ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ያለበት እንዲህ ኣይነቱ የእርዳታ ግኑኝነት ከአመሪካ መንግሥት ጋር ኣያሻኝም የሚል አቋም ሊወስድ ይችላል። የኣገር ሉኣላዊነት ሲደፈር ኣስፈላጊ ከሆነ ለሉኣላዊነት ክብር ያለው መንግስት ዲሞክራሲያዊም ይሁን ኣምባገነን ለባእድ ኣገር ጫና እንደማይንበረከክ ማሳየትና ኣጥብቆ በመቃወም የራሱ እርመጃዎችን መውሰድ ይጠበቅበታል። ኢህወደግም በዚህ እርምጃ ሊወቀስ የሚችል ኣይመስለኝም። ያ ከሆነ ረቂቁ የሚጠይቀው እርምጃና ውጤቱ የእርዳታ ማእቀብ ማድረግ ስለሆን ውጥረቱ በቅድምያ በኣገሪቱ ኢኮኖሚና ተቋማት በተለይም በህዝቡ የሚከሰት ይሆናል። ከዚሁ የሚከተለው ነገር ቀውስና ውድቀት ነው። በተለይም የቻይና ሚና በአፍሪቃና በኢትዮጵያ እየሰፋ ስለመጣ የኢትዮጵያ መንግሥት ከኣመሪካ ጫና ፋታ የሚያገኝበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።

ረቂቁ የተባለለትን ውጤት ሊኖረው የማይችልበት ሌላው ምክንያት ስለ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ መሆኑ ቀርቶ ስለ ኣመሪካ ጥቅምና በኢትዮጵያ ላይ ስለሚኖራት "ህጋዊ" ሉኣላዊነት የሚደነግገው ቁልፍ ኣንቀፅ ክፍል 6፣ ቁጥር 4 (ii) መኖሩ ነው። ማለትም የሰብአዊ መብት እየተረገጠ ባለበት ሁኔታም ፕረዚዳንቱ ህጉ ተግባር ላይ ከማዋል የማገድ ስልጣንን ይሰጣል። ለምን ይሰጣል ማለት ኣይቻልም፣ ኣመሪካ ነውና። ይህ የሚያመለክተው ሌላ ጒዳይ የአመሪካ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የፀረ-ኣሸባሪነት ሽርክና ግኑኝነቱ እስከ ቀጠለ ድረስ HR2003 ተግባራዊ እንደማይሆን ነው።

ዋናው ሌላ የሉኣላዊነት ኣጠያያቂው ጒዳይ ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ከጥገኝነት ነፃ የሆነ የውጭ ፖሊሲ የሚከተል መነግሥት ቢመጣም ፕረዚደንቱ የአመሪካን ጥቅም የሚጠብቅበትን መርሆ

በመከተል ኣልባሌ ምክንያቶችን በመፍጠር የመጫን ህገወጥ እርምጃዎችን እንዲያራምድ እድሉን ይከፍታል።

ለማጠቃለል ያህል ይህ ረቂቅ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ምንም ስፍራ ስለሌለው ዲሞክራሲን ይከስታል ብሎ መጠበቅም የዋህነት ነው። ኢ-ዲሞክራስያዊ የሆኑ የመንግስትና የተቃዋሚዎች ድርጅቶች ባህሪ የመቀየር ሂደት ሊያስከትል ኣይችልም። ዲሞክራሲያዊ ስርኣት ለመመስረት የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ዲሞክራስያዊ ባህል ብቃት ይጠይቃል። እስከዛ ድረስ ግን ኣምባገነን መንግስታት ጠቃሚ ወይም ጎጂ ለሆኑ የውጭ ጫናዎች ጆሮ ዳባ ናቸው።

ኣስተያየት ወደ laekegs@hotmail.com መላክ ይቻላል።